ኮሚኒኬ 5 ጥቅምት 1 ቀን 2011ዓ.ም.

# ኢ.መ.ድ. የኢትዮጵያ ስፔስ ሳይንስ ሶሳይቲ ባዘጋጀው ኤግዚቢሽን ላይ ተሳተፈ

የኢትዮጵያ መድን ድርጅት የኢትዮጵያ ስፔስ ሳይንስ ሶሳይቲ ባዘጋጀው የአለም የሕዋ ሳምንት ክብረ በዓል "በሕዋ ዓለም አንድ ትሆናለች" (**space unites the world**) በሚል መሪ ቃል በኢትዮጵያ ብሄራዊ ባህል ማዕከል በተዘጋጀ ኤግዚቢሽን ላይ መስከረም 27 ቀን 2011 ዓ.ም. ተሳተፈ፡፡

ክብረ በዓሉ በተለያዩ ዝግጅቶች የተከበረ ሲሆን ከፍተኛ የመንግስት ሃላፊዎች እና ጥሪ የተደረገላቸው እንግዶች እንዲሁም የሶሳይቲው አመራር አባላትና የተለያዩ ከጉዳዩ ጋር ግንኙነት ያላቸው ባለድርሻ አካላት መገኘታቸው ታውቋል፡፡

በዕለቱ ዝግጅቱን በንግግር የከፈቱት የኢትዮጵያ ስፔስ ሳይንስ ሶሳይቲ ዋና ስራ አስፈጻሚ ወ/ሮ ቤዛ ተስፋዬ ሲሆኑ ሶሳይቲው ሲመሰረት 1996 ዓ.ም. 47 አባላት ነበሩት:: አሁን ላይ ሶሳይቲው 10,000. የግል & 25,000 የድርጅት አባላት ያሉት ሲሆን 25 ቅርንጫፎችን በመክፈት በመላ አገሪቱ እየተንቀሳቀሰ መሆኑን ገልጸዋል፡፡ ወ/ሮ ቤዛ አያይዘውም የሶሳይቲውን ተግባራት የገለጹ ሲሆን ተግባራቱም አለምዓቀፍ የስፔስ ሳይንስ ሳምንት ለአስር ጊዜ የተከናወነ መሆኑ& በየወሩ ጃንሜዳ ላይ የሶሳይቲው ቴብሳይት ለህዝብ ይፋ በማድረግ የተለያዩ ሳይንሱን በተመለከተ በዓለም አቀፍ ደረጃ የተከናወኑ ተግባራት እንዲጎበኝ በማድረግ በሳይንሱ ዘርፍ የልምድ ልውውጥ ማድረግ እንዲቻል የተደረጉ መሆኑን በመግለጽ ለቀጣይም የስፔስ ሳይንስ ቲያትር ለመገንባት ዝግጅት መጠናቀቁን ገልጸዋል፡፡

የስፔስ ሳይንስ ሶሳይቲ ዓመታዊ ክብረበዓሉን በተለያዩ ዝግጅቶች በማቅረብ የተከበረ ሲሆን ከነዚህም ውስጥ ጥናታዊ ጸሁፎች& የታዋቂ ሰዎች ንግግሮች እንዲሁም የተለያዩ ድርጅቶች አውደርዕይ የቀረበ ሲሆን ድርጅታችንም በአውደ ርዕዩ ላይ ተሳታፊ በመሆን ለሶሳይቲው አባላትና ጥሪ ለተደረገላቸው እንግዶች ስለ መድን ድርጅት አገልግሎትና ጠቀሜታ በኢንተግሬትድ ኮሚኒኬሽን ቡድን አባላት በሰፊው ማብራሪያ የተሰጠ ሲሆን ድርጅቱን ሊያስተዋውቁ ይችላሉ ተብሎ የታመነባቸው ልዩ ልዩ የስጦታ ዕቃዎች እንዲሁም የተለያዩ የመድን ብሮሸሮች& የድርጅቱ አጭር መግለጫዎች እና መጽሄቶች ለጎበኚዎች ተሰጥቷል፡፡





የስፔስ ሳይንስ ሶሳይቲ ኤግዚቢሽን ገጽታ በከፊል